# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 4- 6 ታህሣሥ / የካቲት 1990


## ከአዘጋጅ ብዕር

የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ ሥርጭቱን የጀመረው መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ነው።

ይህ ሁለተኛ መጽሄት የሚቀርበው ሬዲዮው ከጀመረ ከስድስተኛው ወር በኋላ ስለሆነ በቅርቡ ከተላለፉትና ባጭሩ ከቀረቡት የተወሰኑ ዜናዎች ሌላ፤ የመጽሄቱ ዋና ይዘት ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት ለሰጡ ትችቶች፤ ትንተናዎች ወዘተ ነው።

መልካም ንባብ !


* ክሊንተን አፍሪካ........................1
* የፖለቲካ አጥቂነት.....................2
* በአንድ ራስ አንድ ምላስ.........3
* ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ኬንያ.......5
* የእብዶች ሎጂክ ........................6
* በ 1992ቱ ምርጫ ላይ የተጠነሰሰው ሤራ.....................7
* ህወሀት ለምርጫ ይዘጋጃል፤ ተቃዋሚዎችስ?.......................8
* የወያኔ መሰንበቻ ስልት...........10
* ከጋዜጦች አምድ.................... 11
* ዘመናዊ ባርነት...................... 15
* የወያኔን ኢትዮጵያ ሾላ በድፍን........................17


ቀስተ ደመና (Radio Rainbow) የሰላምና የውንድማማችነት ድምፅ ሬዲዮ
በአጭር ሞገድ(short wave) እንደሚከተለው ይተላለፋል ፤

| ቀን | ሞገድ | ሰዓት | አቅጣጫ |
|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 19 ሜትር ባንድ<br>15.365HZ | በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር<br>ከምሽቱ 1 እስከ 2 ሰዓት | ምስራቅ አፍሪካ<br>ኢትዮጵያ |
| ዓርብ | 31 ሜትር ባንድ<br>9855kHz | በአሜሪካ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00p.m. - 10.00pm | ሰሜን አሜሪካ<br>ምስራቃዊ ጠረፍ |
| እሁድ | 49 ሜትር ባንድ<br>5.910kHz | በአውሮፓ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00a.m-10.00am (10.00-11.00a.m ለብሪታንያ ) | ምዕራብ አውሮፓ |


አድራሻችን፤
አስተያየት፤
ትችት፤ ወዘተ
ካላችሁ,

Radio Rainbow ,
c/o P.O .Box 140104
53056 Bonn , Germany
Fax : 0049 228 612381



GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA

Groupe de Recherche et d'Action pour la paix en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique

Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa

ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

1ኛ + የምርጫው ግዜ ከመቃረቡ ቀደም ብሎ ነፃውን ፕሬስ በማኮላሸት በዚያ ወቅት ምንም ዓይነት የረባ የተቃውሞ ድምጽ የማይሰማበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

2ኛ + ተቃዋሚ ኃይሎች ለነጻ ምርጫ መሳካት ያቀረቧቸው ዓለም አቀፋዊ ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ምርጫው እንዲካሄድ

3ኛ + በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ ከሚገኙ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ጋር በሚስጥር በመደራደር ካለፈው ሻል ባለ ሁኔታ የመንቀሳቀስ መብት ታውቆላቸው በምርጫው እንዲሳተፉ መፍቀድና በመጪው ፓርላሜንት ውስጥ የተወሰነ ወንበር እንድያገኙ ከወዲሁ ዋስትና መስጠት

4ኛ + የኢህአዴግ የምርጫ ቦርድ ካለፈው ይበልጥ ተዓማኒነት ያለው ውጤት እንዲያቀርብ ባለው እቅድ መሰረት በጠቅላላው በምርጫ ለሚሳተፉት ተቃዋሚ ኃይሎች ከመንግሥት በተቆረጠላቸው መሠረት እስከ 20 በመቶ ድረስ ከፓርላሜንቱ ወንበር ሊይዙ የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያመቻች

5ኛ + አዲስ በሚመረጠው ፓርላሜንት አንድ አምስተኛውን ወንበር በመያዝ እነዚህ ኃይሎች አናሳም ቢሆኑ የተደራጀ ፓርላሜንታዊ ተቃዋሚ ኃይል ሆነው እንዲቀርቡ ማገዝ

6ኛ + በውጭ ሃገር ለእንደዚህ አይነቱ እቅድ ተባባሪ ለመሆን አሰፍስፈው የሚገኙ አንዳንድ ኃይሎች ባስቸኳይ ወደ ኃገር ተመልሰው ሥራቸውን እንዲጀምሩ መርዳት፤ በሃገር ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚዎች ላይ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የጭቆና እርምጃዎችን በማድረግ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዲደረግና ባእዳን መንግሥታትም በዚህ ግፊት የበኩለቸውን እንዲረዱ መጠየቅ የሚሉ ነጥቦች ይገኙብወታል።

--------------////--------------

## ህወሃት ለምርጫው ዝግጅቱን ጀምሯል። ተቃዋሚዎችስ?

ወያኔ ከዳር እስከዳር የሚቆጣጠረው መጪው ምርጫ ከወዲሁ ለተቃዋሚ ተብዬዎች ሃያ ከመቶ ውጤት ለመስጠት እየተመቻቸ ነው። ይህ እርኩስ እቅድ ከወዲሁ ሳይጋለጥ ከተሳካ......... መጨረሻውን አሁን ማንም ሊያየው ለማይችል ረዥም ግዜ ይች አገር እጅግ ውስብስብ የሆነ የፈተና ወቅት ውስጥ ትገባለች። ይህንን አደጋ ለመቃወም........... አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ስለ ነጻ ምርጫ 'ለአዲስ ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ' በሚል ሰነድ ያቀረባቸውን [ተቃዋሚ ኃይሎች ]....... ተቀብለው...... በኢትዮጵያም ህዝብ ፊት ሆነ በዓለም አቀፍ ኮሚኒቲ ፊት ግልጽና ዴሞክራሲያዊ አማራጫቸውን ይዘው በጋራ መታገል አለባቸው።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የነጻ ምርጫ መስፈርቶችን አስመልክቶ የተሰናዳው ሰነድ አንድን ምርጫ ነፃና ሃቀኛ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ከወዲሁ በቅድሚያ የተቆረጠ

ውጤት እንዲያስገኝ ሁኖ አለመመቻቸቱ ነው። ሰነዱ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው ማንኛውም ምርጫ አንድ የተፈለገ ውጤትን እንድያመጣ ከተመቻቸ ወይም በሰነዱ ቋንቋ ‘ሪዛልት ኦሪየንትድ’ ከሆነ በምንም አይነት ነጻ ምርጫ ሊባል አይቻልም።

ወያኔ ከዳር እስከዳር የሚቆጣጠረው መጪው ምርጫ ከወዲሁ ለተቃዋሚ ተብዬዎች ሃያ ከመቶ ውጤት ለመስጠት እየተመቻቸ ነው።

ይህ እርኩስ እቅድ ከወዲሁ ሳይጋለጥ ከተሳካ በሃገራችን የሰላምና የዴሞክራሲ ጉዳይ ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚወድቀው ምርጫውን በሚከተሉት አምስት አመታት ብቻ አይደለም። መጨረሻውን አሁን ማንም ሊያየው ለማይችል ረዥም ግዜ ይች አገር እጅግ ውስብስብ የሆነ የፈተና ወቅት ውስጥ ትገባለች።

ኢህአደግ በፓርላሜንቱ ውስጥ ከ99 ከመቶ እየተቆጣጠረ እንኳን በዚች ሃገር ነጻ ምርጫ አካሂጃለሁ፤ ደሞክራሲን አስፍኛለሁ እያለ የሚያወናብድ አይነ ደረቅ ኃይል ነው። ከሱም አልፎ አንዳንድ እውር ድጋፍ የሚለግሱት ባእዳን ሳይቀሩ አሁን ባለው ሁኔታ እንኳን የደሞክራትነትን ሰርቲፊኬት ሲለግሱት እናያለን። ከዚህ ሃቅ ስንነሳ አሁን ባለው እቅድ መሠረት አንዳንድ ተቃዋሚዎች በስግብግብነትም ሆነ እጃቸው እየተጠመዘዘ ከመንግሥት ጋር በቅድሚያ በተቋረጡበት የወንበር ልክ መሠረት በመጪው ፓርላሜንት ውስጥ በተቃዋሚነት ከተሰየሙ ለመጪው ትግል ምን ያህል ውጥንቅጡ የወጣና አስቸጋሪ ሁኔታ እንደሚፈጠር ማየት እጅግ አሸጋሪ አይመስለንም።

ይህንን አደጋ ለመቃወም የሚቻለው በአንድ ዘዴ ብቻ ነው። ኢህአደግ የምርጫ ፌዝ ዝግጅቱን ጀምሯልና ተቃዋሚ ኃይሎችም በጋራ አጸፋውን ለመስጠት ዛሬ ነገ ሳይሉ በህብረት መነሳት አለባቸው። ይህ አጸፋ ምርጫው ጥቂት ወራት ሲቀረው ሽብ ረብ የሚሉበት ሌላ ፌዝ መሆን የለበትም። አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ስለ ነጻ ምርጫ ‘ለአዲስ ደሞክራሲያዊ ጅማሮ’ በሚል ሰነድ ያቀረባቸውን ዓለም አቀፋዊ ቅድመ ሁኔታዎች እንዳለ ተቀብለው ወይም ደግሞ ከሱ ላይ የሚጣለውን ጥለው የጎደለውን አሟልተው ነጻ ምርጫ ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ በኢትዮጵያም ህዝብ ፊት ሆነ በአለም አቀፍ ኮሚኒቲ ፊት ግልጽና ደሞክራሲያዊ አማራጫቸውን ይዘው በጋራ መታገል አለባቸው።

በዚህ መልክ በጋራ ከታገሉ ኢህአደግ ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶችን ተቀበለ አልተቀበለ፤ ከምርጫውም በፊት ሆነ ከዚያ በኋላ ለሚመጣው ቀጣይ ትግል እጅግ አመች ሁኔታ ይፈጥራሉ።

ይህ ትግል ከተካሄደ በምርጫው ወቅት በሻማ ያኸነት፤ ከምርጫ ተብዬው ሂደት በሚፈልቀው ፓርላሜንት ውስጥ ደግሞ በሥነ ሥርዓት አድማቂነት በመቆም አውቀውም ሆነ ሳያውቁ በዚህ ሤራ ለመሳተፍ ያሰፈሰፉትን ኃይሎች ነገሩን ቆም ብለው እንዲያስቡበት ይገፋፋቸዋል። አሻፈረን ብለው ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ የወንበር ልክ ብቻ ተቋርጠው በዓላማቸው ከቀጠሉም ደሞክራሲያዊ ኃይሎች ባደረጉት የጋራ ትግልና ባቀረቡት የጋራ አማራጭ ሳቢያ ማንነታቸው ተጋልጧልና ከምርጫው በኋላ በህዝባችን መንፈስ ሊከተል የሚችለውን አደገኛ ውዥንብር እጅግ ይቀንሰዋል።

ይህ ትግል ከተካሄደ ሌላም ከፍተኛ ጥቅም አለው። ‘ኢህአደግ በምንም አይነት ነጻ ምርጫን ስለማይቀበል’ በሚል ሰበብ የፖለቲካውንና የዲፕሎማሲውን ትግል የሚያቃልሉና እንደ አጉል ግዜ ማጥፋት የሚቆጥሩ በትጥቅም ሆነ በሰላማውዊ የትግል መስክ የተሰማሩ ጽኑ ተቃዋሚዎችም ግልጽና ደሞክራሲያዊ የጋራ አማራጭ ይዘው መታገላቸው ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ሊስቱት አይገባም።

በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት በነጻ ምርጫ ጥያቄ ዙሪያ በጋራ ቢታገሉ ዛሬም ሆነ በህድረ ምርጫው ዘመን የሚያካሄዱት ጸረ ኢህአደግ ትግል ከጦር ጠማሽነትም ሆነ ከአክራሪነት ዝንባሌ የመነጨ ሳይሆን፤ ወይም ደግሞ እጅግ ከባድና የማይመስል ጥያቄ ሳይሆን ድፍን አፍሪካን ባማላበስ ላይ ያለውና / የወያኔ ባእድ ደጋፊዎችም እናምንበታለን የሚሉት / የዴሞክራሲና የነጻ ምርጫ ጸጋ ለህዝባችንም ይድረሰው የሚል ህዝባዊ ዓላማ

አንግበው የተነሱ መሆናቸውን በግልጽ ያሳዩበታል። ይህ ጥራት የሚያመጣውን አወንታዊ አስተዋጽኦ መገመት አስቸጋሪ አይመስለንም።

የጋራው ትግል አገልግሎቱ ውኸንብሩን በማጥፋት አይወሰንም በጋራው ትግል መድረክ ሳቢያ የሚገኘው መቀራረብ ፤ መተጋገዝና አብሮ የመሥራት ልምድ ለቀጣዩ ትግልም እጅግ አመቺ የሆነ ሁኔታ ይፈጥራል።

ባጭሩ ሴራው ጀምሯልና የማክሸፉን ትግል ዛሬ ነገ ሳንል እንጀምረው እንላለን። ሴራው ይክሸፍ ስንል ደግሞ ዋናው ጥያቄ እስከዚህም ድረስ የኢህአዴግን የፌዝ ምርጫ ሂደት የማቆም ወይም ያለማቆም ጥያቄ አይደለም። በጋራ ትግልና ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ሥር በመሰማራት የኢህአዴግን ሤራ ማጋለጥ፤ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ በምርጫው ሊሳተፉ የሚሞክሩትን ኃይሎች የታሰበውን ውኸንብር እንዳይነዙ መከላከል፤ የአገዛዙም ባእዳን ደጋፊዎች ዓይን እስካላቸው ድረስ አላየንም፤ ጆሮ እስካላቸው ድረስ አልሰማንም የማይሉበት ሁኔታ መፍጠር ከቻልን ለመጪው ትግል ሁኔታዎችን ማመቻቸታችን ስለሆነ ወያኔ የመረጠውን ጎዳና ቢመርጥ እኛ ከወዲሁ የማይናቅ ድል ተቀዳጅተናል ማለት እንችላለን።

--------------////--------------

# የወያኔ ኢህአዴግ
# የመሰንበቻ ስልት

ከጌታቸው በንቲ፤ ጂማ

ወያኔ ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ ለመሰንበት የሚከተላቸው ስልቶች ብዙ መልኮች ያሏቸው ቢሆኑም ሁለቱ ግን በተደጋጋሚ የሚስተዋሉ ናቸው።

የወያኔ ኢህአዴግ አንዱ መላ የባእዳን አገሮች የሚወዱትን ተግባር ማከናወን ነው። በዶላር፤ በምክር፤ በትራንስፖርት፤ በጦር መሣሪያና፤ በዘመናዊ የቴክኖሎጂ መገልገያዎች ጡንቻውን ለሚያፈረጥሙለት፤ ባዕዳን ኃይሎች የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት ጦር አንስቶ እስከመፋለም ድረስ አገልግሎቱን ይሰጣል። ሌላው ቀርቶ ከጎረቤት አገሮች ጋር ጠብ ያለሽ በዳቦ እያለ አጋሮቹ በሚሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ድንበር እየጣሰ ወረራ ያካሄዳል።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ሠላም ፍትህ ሕዝባዊ ሥርዓት የሰፈነባት አገር ናት እያለና አጋሮቹንም እያሰኘ፤ ባገሪቷ ውስጥ ማንም ዜጋ የተቃውሞ ድምፅ እንዳያሰማ፤ የፖለቲካ ድርጅቶችም አማራጭ ሥርዓተ መስተዳደር እንዳያቀርቡ፤ ጋዜጦች ሞልቶ የሚፈሰውን ሥቃየ ሕዝብ ዘግበው እንዳያሰራጩ በእስራትና በጥይት ፀጥ ያደርጋል። ስለሆነም በኢትዮጵያ በጠበንጃ አፈሙዝ ተገዶ የተዘጋ ልሣን እንጂ በሰብአዊ መብቶች ዋስትና ተበረታቶ የሚናገር ነፃ አንደበት የለም። ኢትዮጵያ ዝም ፀጥ ሁሉም እንቅስቃሰ ። እረጭና ቀጥ ያለባት አገር ሆናለች። የወያኔ+ኢህአዴግ የአዋቂ አጥፊ አገሮች ይህን በአባዜ ብዛት የተገኘውን ዝምታና ፀጥታና አፋቸውን ሞልተው “ሠላም ነው፤ የዴሞክራሲ አስተዳደር ውጤት ነው” ይላሉ።